የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፫
አዲስ አበባ – መስከረም ፲፩ ቀን ፲፱፻፺፯

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

11th Year No. 3
Addis Ababa 21st September, 2004

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፲፫/፲፱፻፺፯ ዓ.ም
የላሊበላ ኢንጅነሪንግ ኮንስትራክሽን ድርጅትን ለማፍረስ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ............ ገጽ ፪ሺ፱፻፲፯

## CONTENTS

Council of Ministers Regulation No 113/2004.....
Dissolution of Lalibela Engineering & Construction Enterprise Council of Ministers Regulation ............................................Page 2917

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፲፫/፲፱፻፺፯ የላላበላ ኢንጅነሪንግ ኮንስትራክሽን ድርጅትን ለማፍረስ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት ልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯//፩/ሐ/ መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል ።

፩· **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የላሊበላ ኢንጅነሪንግና ኮንስትራክሽን ድርጅትን ለማፍረስ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር፻፲፫/፲፱፻፺፯"ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· **መፍረስ**

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፶፯/፲፱፻፹፮ ተቋቁሞ የነበረው የላሊበላ ኢንጅነሪንግ ኮንስትራክሽን ድርጅት በዚህ ደንብ ፈርሷል።።

፫· **የመብትና ግዴታ መተላለፍ**

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፶፯/፲፱፻፹፮ ተቋቁሞ የነበረው የላሊበላ ኢንጅነሪንግ ኮንስትራክሽን ድርጅት መብትና ግዴታዎች በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፵፭/፲፱፻፺፩ ለተቋቋመው የቃሊቲ ኮንስትራክሽን ዕቃዎች ማምረቻ ድርጅት ተላልፏል።

፬· **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከነሐሴ ፳፭/፲፱፻፺፮ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ መስከረም ፲፩ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ጠቅላይ
ሚኒስትር

## *COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No.113/2004 COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO PROVIDE FOR THE DISSOLUTION OF LALIBELA ENGINEERING & CONSTRUCTION ENTERPRISE*

This Regulation is issued by the Council of Ministers Pursuant to Article 5 of the Definition of Power and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995 and Article 47/1/ /c/ of the Public Entepprises Establishment Proclamation No. 25/1992.

1. *Short Title*

   This Regulation may be cited as the "Dissolution of Lalibela Engineering and Construction Enterprise'' Council of Ministers Regulation No 113/2004

2. *Dissolution*

   Lalibela Engineering & Construction Enterprise established under the Council of Ministers Regulation No. 157/1994 is hereby dissolved:

3. *Transfer of Rights and obligations*

   The rights and obligation of Lalibela Engineering and Construction Enterprise established under the Council of Ministers Regulation No. 157/1994 are hereby transferred to Kality Construction Materials Production Enterprise Established under Council of Ministers Regulation No. 45/1998.

4. *Effective Date*

   This Regulation shall come into force as of the 31st day of August 2004.

Done at Addis Ababa 21st day of September

Meles Zenawi
Prime Minister of the Federal Democratic
Republic of Ethiopia

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001